# የእኛይቱ ባርጩማ

ከበላይ ተሰማ

ከቶ እነማናችሁ ተቀናቃኞቹ
የእኛይቱን ባርጩማ ተቃዋሚዎቹ
ሦሥት ደቂቃ ብቻ በማምንት ተናግሮ
በወር የሚሠጠን $5ሺ መንዝሮ
ከቶ የት ይገኛል ደግ እንደ ፓርላማ
መጠይቁ አድርባይ ወንበሩ ባርጩማ።

ሆይ ጉድ!
አብዳችኋል እንዴ?ምን ታወራላችሁ
የፓርላማን ወንበር ከባድ ሥራ አርጋችሁ
ብር መዛቅ ሲቻል ለመለስ አድራችሁ
እንደ እኛ ባርጩማ የት ታገኛላችሁ?

ኧረ ተው ታቀቡ እስቲ እንኑርበት
ለሆዳችን ተገዝተን አርፈን ቁጭ ባልንበት
የናንተ መንጫጫት እኛ ሥንሰግድለት
ባርጩማው ምቹ ነው እናንቀላፋበት
ሕዝቡ እንደሁ አይነሣ ታሥሮ በሠንሠለት
ዕድሜ ለመለሰ እንዘፍዘፍበት ።